# ከአቶ ስለሺነህ የደረሱን የመጀመሪያ ተከታታይ እ-ጦማሮች።

፩) በስመ፡አብ፡ወወልድ፡ወመንፈስ፡ቅዱስ፡፩፡አምላክ፣

በስመ፡እግዝእትነ፡ቅድስት፡ማርያም፡ወላዲተ፡አምላክ፤ሃሌ፡ሉያ!፡ሃሌ፡ሉያ!።ሃሌ፡ሉያ!፡አሜን።

ለተከበሩት፡ኢትዮጵያዊው፡ወገኔ፣ንቡረ፡እድ፡ኤርምያስ፡ከበደ፡ወልደ፡ኢየሱስ፤

ከሥራ፡አጋሮችዎ፡ጋራ፡ሰላም፡እና፡ጤናን፡እመኝላችኋለሁ።

ከሰላምታዬ፡ቀጥዬ፡የማቀርበው፡ጥያቄ፡ለአንዲት፡እመቤት፡ጥቁር፡ክር፡ማለትም፣ማተብ፡አንገት፡ላይ፡ስለ፡ማሠር፡በሰጡት፡መልስ፡ይሆናል።

በመጽሐፍዎ፡ነጭ፡ልብስ፡መልበስ፡የኀዘን፡ነው።የግብፁ፡ጳጳስ፡በአገራችን፡የቤተ፡ክህነት፡መሪ፡ስለ፡ነበሩ፣አለባበሳችንን፡እንዲቀዬር፡እና፡ልጹሕ፡ኢትዮጵያዊቷን፡ቀዳሴ፡መዓዛን፡ደግሞ፡አልፎ፡አልፎ፡ካልሆነ፡በስተቀር፡እንዳይቀደስባት፡አደረጉብን።ጥቁር፡ልብስ፡መልበስ፡ግን፡የደስታ፡ነው።ያሉ፡እና፡በተግባርም፡ነፍሱን፡ይማርና፡የበኩር፡ልጅዎ፡ዕረፍት፡ግዜም፡የኀዘን፡ሥርዓተ፡ጸሎታችሁን፡ነጭ፡በመልበስ፡እንዳከናወናችሁ፡የተገለጸ፡መሰለኝ።ስለዚህ፣ጥቁር፡ክር፡ወይም፡ማተብ፡ለእመቤቷ፡በሰጡት፡መልስ፡የዲያብሎሳዊ፡መንፈስ፡እርኩስ፡አምልኮትን፡እንደ፡እሚገልጽ፡የሆነበት፡ስለ፡ተምታታብኝ፡ነው።ይኸውም፦አረንጓዴ፣ብጫ፣ቀዩ፡ክርስትና፡ፈትላችንን፡በአንገታችን፡ማሠሩ፡እንደ፡ተጠበቀ፡ሁኖ።

፪) ክቡር፡ንቡረ፡እድ፡ኤርምያስ፡ከበደ፡ወልደ፡ኢየሱስን፡ያሰንብትልን፡በማለት፡ከአስተዋወቁት፡ጓደኞቼ፡ጋራ፡እያመሰገነ፡ይገኛል።ከመጽሐፍ፡የበለጠ፡ለክፉውም፡ለደጉም፡መኻር፣አጽናኝ፣ያለውን፡የእማይነፍግ፡ለጋሥ፡እና፡ታማኝ፡የለም።አንዱ፡ደራሲ፡ተሌላው፡ቢለያይም፣የደራሲውን፡ማንነት፡ለመረዳት፡ደግሞ፣የአንባቢው፡ትጋት፡እና፡የመማር፡ፍላጎት፡ሲኖር፡በበለጠ፡ያኮራል።

በጎዋ፡ሰሌዳችሁ፡የእምታስተምሯቸው፣ሰሚ፡ጆሮ፡እና፡አንባቢ፡አንጀበት፡ካለ፤ለሀገር፡እና፡ወገኖቻችን፡የወደ፡ፊትም፡ቋሚ፡ቅርሶች፡ስለ፡ሆኑ፡እግዚአብሔር፡የድካማችሁን፡ወረታ፡ይክፈላችሁ።

ሰሞኑን፡በአመሪካ፡ነፋስ፡ድምፅ፡ለላል፡ይበላል፡ጐብኝዎች፡የቤተ፡ክርስቲያኖቻችንን፡በብራና፡የተጻፉ፡ጸሎት፡ምጽሐፎች፡በ፡፲፰፡ብሮች፡ይሸጣሉ።ይኸንም፡የተመለከቱት፡ጐብኝ፡ሴት፡እንዴት፡የሀገሪቱ፡ቅርስ፡በእንደዚህ፡ዓይነት፡ሁኔታ፡ይወድማል!፡ብለው፡ለእሚመለከተው፡ባለ፡ሥልጣን፣የሀገሪቱ፡ቅርስ፡እንዲጠበቅ፡ማሳሰቢያ፡ለመጻፍ፡በዝግጅት፡ላይ፡መሆናቸውን፡ሰምቶ፡ስለሺነህ፡በጣም፡አዘነ።የእግዚአብሔር፡ትዕግሥት፡እስተ፡መቼ፡ይሆን?።በጉያ፡መጽሐፉ፡እንደ፡ተገለጸው፣የኃጢአታችንን፡ብዛት፡ተገንዝበን፡ንሥሐ፡እንድንገባ፡ምልክቶች፤በመሬት፡መንቀጥቀጥ፡መውደም፡በሀይቲ፣በላቲን፡አመሪካ፣በጃፓን፣በአመሪካ፣በቻይና፡....ወዘተ፡እንደ፡ገና፣በጐርፍ፡አልቂት፡-በሕንድ፣በአመሪካ፣በፊሊፕን፣በታይላንድ፡እና፡ቻይናን፡መሰሎቹ።በመሬት፡እንቅጥቅጥም፡ጃፓን፡እና፡ቻይና፡በዬግዜው፡የመጠቃት፡ልምድ፡ቢኖራቸ

ውቻ፤አሁን፡ደግሞ፣በእሳተ፡ገሞራ፡በበረዶ፡መሬት፡(አይስላንድ)፤በተፈጠረው፡ጢስ፡ጥቁር፡ጉም፡ አየሩን፡ስለ፡ሸፈነው፡የአየር፡ሠረገላዎች፡በየቦታው፡እንዳይበሩ፡ተደርገዋል።የአየር፡ሠረገላ፡ ከምንግዜውም፡በሸፈ፡እየተከሰከሰ፡ብዙ፡ሕዝብ፡ያልቃል።ሊባኖን፡በአቫዥ፡ሀብታሙ፡አብራሪነት፡ በተከሰከሰው፡የወጣት፡ኢትዮጵያውያን፡ሕይወት፡ማለፉ፤የፖላንድ፡መሪ፡ከባለቤታቸው፡እና፡ ከሥራ፡አጋሮቻቸው፡ምሉክዎች፡ጋራ፡ሕይወት፡ማለፍ፡ለማስረጃነት፡የእሚጠቀሱ፡ሰቆቃዎች፡ ናቸው።ይኸ፡ሁሉ፡ሲሆን፣የሰው፡ልጆች፡ነግ፡በእኛ፡ነው፡እና፡እግዚአብሔር፡በሠራነው፡ኃጢአት፡ ይቅር፡በለን፡እያልን፡በማንጋጠጥ፡እጆቻችንን፡ለመዘርጋት፡በትዕቢት፡መወጠራችን፡እጅግ፡ ያሳዝናል።ዓይኖቻችን፡እያዩ፡ንሥሐ፡ሳንገባ፡ማለፈችንም፡ለሌላው፡ቋሚ፡ወገን፡ፀፀት፡አሸናናቢ፡ ሁኔታ፡ይሆናል።

ሙቶ፡የተነሣ፡ሁለትኛ፡ሞትን፡አይመኝም።ጌታ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ፡ከመካከላችን፡ሆኖ፡ ንሥሐ፡ግቡ።ወደ፡እግዚአብሔር፡መንግሥት፡ፊታችሁን፡አዙራችሁ፡ጸልዩ።እንደ፡እሚል፡ስለ ሺ፡ነህን፡ይሸማዋል።እግዚአብሔር፡ብርሃን፡መሆኑንም፡ተነግሮናል።፡ብርሃኑን፡እንዳናይ፡ግን፡ ዲያብሎስ፡ዓይኖቻችንን፡የጋረደን፡መሆናችንን፡አልተገነዘብነውም።እናም፣ወደ፡ንጹሕ፡ኅሊ ናችን፡እንድእንመለስ፡ልቦና፡ይስጠን።

በቅርቡ፡በጎዋ፡ሰሌዳ፡የፊት፡መጽሐፍ፡ቡድን፡ስለሺ፡ነህ፡አባል፡ሁኖ፡የሥነ፡ጽሑፉችንን፡ በተመለከተ፤የሥነ፡ሥርዓተ፡ነጥቦች፡አጻጻፉችን፡ሕገ፡ሰዋሰው፡ባሕላቸውን፡ስለ፡ሳቱ፡እንደ፡ጥን ቶቹ፡ጠብቀን፡ቅርስ፡እድናተርፍ፤ለመማማር፡ዐቅዶ፡ለውይይት፡አቅርቦ፡ነበረ።ነገር፡ግን፡እርሱ፡ ስሕተተኛ፡እንደ፡ሆነ፡ተደርጐ፡ለደረሰው፡መልስ፡በደስታ፡ተቀብሎ፡በመከራከር፡እያገገመ፡ነው። ሆነና!ጠለቅ፡ብሎ፡ሲያስበው፣በዬጎዋ፡ሰሌዳዎች፡ከእሚጻፉትም፡ሆኑ፡በመጽሐፍ፡ውስጥ፡ለዋቢነት፡ አቅርቦ፡መከረከሪያ፡በማጣቱ፡ወደ፡ጥንት፡ደራሲዎች፡መጻሕፍት፡ጠቀሳ፡ገብቶ፡ለግዜው፡መርታት፡ ችሏል።የእርስዎንም፡መጻሕፍት፡ለነዚህ፡ዋቢ፡ለማድረግ፡ባለ፡መቻሉ፡ጥልቅ፡ኀዘኔታ፡ ተሰምቶታል።ይኸን፡ሲያሽብ፣ነጋድራስ፡አፈወርቅ፡ገብረ፡ኢየሱስ፣ዳግማዊ፡ምኒልክ፡በእሚሰኝ፡ ርእስ፡በጻፉት፡ውስጥ፤አለቃ፡ታዬ፡ገብረ፡ማርያም፡የዳግማዊ፡አፄ፡ምኒልክን፡ታሪክ፡ሊጽፉ፡ነው። እየተባለ፡ሰምተው፡ያሉት፡ትዝ፡አለው።"ታዬ፣ብልህ፡ጸሐፊ፡ነው።......ሲጽፍ፡አማርኛውን፡ አሳምሮ፤ለንግድ፡ሥራ፡የእሚስማማውን፣ለመንግሥት፡ሥራ፡የእሚስማማውን፡ሌላውንም፡ለይቶ፡ .........ወዘተ፡አጣርቶ፡በጥንቃቄ፡ቢጽፈው፡ይሻላል።ችሎታው፡የለኝም፡እንጂ፣እኔ፡ብጽፈው፡ ምንኛ፡በታደልኩ፡ነበር።........."፡ነጋድራስ፡አፈወርቅ፡ገብረ፡ኢየሱስ፡ገበሬው፡እና፡ነጋዴው፡ ሕዝብ፡እንዲማር፡ይጥሩ፡ነበር፡ይባላል።እነዚህ፡በግብርና፡እና፡ንግድ፡የተሠማሩት፡የእሚናገሩት፡ ኢትዮጵያኛ፡(ዐማርኛ)፡ስለ፡ሆነ፡የአፄ፡ምኒልክን፡ታሪክ፡አንብቦ፡እንዲረዳቫቸው፡በመፈለግ፤ ግዕዙን፡ለቤተ፡ክህነት፡መገልገያ፡ብቻ፡እንዲሆን፡ወደው፡ነው።

ሥራ፡እንደ፡እሚበዛብዎ፡እና፡የግዜ፡እጥረት፡እንደ፡እሚኖርብዎት፡ይታወቃል።እርስዎም፡ ከደከሙ፡አይቀር፡ግን፡ረጋ፡ብለው፡ሥርዓተ፡ነጥቡን፡ያሟላ፡የመማሪያ፡መሖሪያ፡እዲሆን፡ቢደረግ፡ ጥንታዊ፡ቅርስነቱን፡አጉልቶ፡ያሳያል።እኛው፡ተጠንቅቀን፡እዬጻፍን፡ወጣቱን፡ትውልድ፡ ካላበረታታነው፡ኢትዮጵያኛው፡እንዲጠፋ፡የእሚሖኙ፡ጠላቶቻችን፡እያሌ፡ናቸው።እናም፣ ልናደርገው፡በእምንችለው፡እጃችንን፡ለሸንፈት፡ዳርገን፡ማንሣት፡የለብንም።ግዜ፡ለመሻማት፡ ተብሎ፡ባሕላችን፡መበላሻ፡መንደርደሪያ፡በር፡አንከፈት።በቀን፡፳፬፡ሰዓቶች፡የሥራ፡ማሽና ዎኖዎች፡አሉን።ዕቅድ፡አውጥተን፡ብንረዳዳ፡የእማንፈጸመው፡ጉዳይ፡የለም።የእማንረዳዳ፡ከ ሆን፡ደግሞ፣ለግል፡ምድራዊ፡ጥቅማቸው፡ብለው፡ዘላለማዊዎች፡ቅርሶቻችንን፡እና፡ሀገራችንን፡ ከእሚያወድሙ፡በምን፡እንለያለን?።ስለሺ፡ነህ፡ጽሑፍቸውን፡በጎዋ፡ሰሌዳው፡ይከታተል፡የነበሩ፡ እና፡ለምን፡ሥርዓተ፡ነጥብ፡አልባ፡ትጽፉላችሁ?።ብሎ፡ጽፎላቸው፤የመቀመሪያውን፡አጠቃቀም፡

ያለ፡ማወቅ፡ችግር፡እንደ፡ሆነ፡ገልጸውለ፟ታል።እሱም፣”መፍታት፡ሳለ፡መምታት?”፡ብለው፡ ሽማግሌው፡ባል፡እኛ፡ሚስቱን፡እንዳስታረቁ፡ሁሉ፡ሲገ፟ረም፡ቀ፟ይቶ፤ለእሹ፡ልከውለት፡ እንዲአስተካክልላቸው፡ጠይቀውት፡ተስማምቷል።እኛም፡በአሐያየቃቸው፡”ሲሻኝ፡ጢስ፡ወጋኝ”። እንደ፡እሚሉት፡ሆኖለት፡ተደሰ፟ቷል።

የእኛ፟ንተንም፡የጎዋ፡ሰሌዳ፡ስለሺ.ነህ፡በማስተዋወቅ፡ላይ፡ነው።መልእክታችሁንም፡በፊት፡ መጽሐፍ፡(ፌስቡክ)፡በእሚሉት፡ብታስተላልፉት፡መልካም፡ነው፡ይላል።በተለይ፟፣በኢትዮጵያኛው፡ ግራ፡ለእሚጋ፟ባው፡ወጣ፟ት፡ትውልድ፣”ኢትዮጵያ፦የዓለሙ፡መ፟ፈረጃ፟ን!”፡ገዝቶ፡በመጀ፟መሪያ፡ እንዲያነብ፟፡እ.ጠማራችሁን፡ሰጥቶ፡በመጋበዝ፡ላይ፡አለ።ሥርዓተ፡ነጥቦችን፡ተከ፟ትሎ፡በመጠ፟ቀሙ፡ ስሕተተኛ፡ነህ፡ሲ.ባል፡በትዕግሥት፡እንዲጽናኛ፡የታወ፟ሰችው፡የክቡር፡ንቡረ፡እድ፡ኤርምያስ፡ከበ፟ደ፡ ወልደ፡ኢየሱስ፡እቤታቸው፡ለተጋበ፟ዘ፡እንግዳ፡የተረ፟ኩለት፡ስለ፡ነበረች፡ከል፟ብ፡አመስግኗቸዋል። እርሷም፣”መቀዬት!፣እረ፡መቀዬት!፣አንቺ፡መቀዬት!”፤ነበረች።እኛም፣እንዲገ፟ነዘቡለት፡ከ፪ቱ፡ ሰወች፡ያገኘውን፡መልስ፡ብቻ፡እኛ፟ሆ!፦

፩ኛ፦በነገራችን ላይ በአማረኛ ጽሑፍ ታይፕ ስታደርግ በየቃላቶች መሀከል ላይ ሁለት ነጥብ አይደረገም ለዛም ነው አብዛኛውን ጊዜ የማናደርገው።እርግጥ ወረቀት ላይ በምንጽፍበት ጊዜ እንጠቀማለን። በአማረኛ የተጻፉ መፅሃፎችን ያየን እንደሆን በሁለት ነጥብ አይጠቀሙም። ለዛም ነው ሁለት ነጥብን ችላ የምንለው። ለማንኛውም መልዕክትህ ገብቶኛል አመሰግናለሁ።

፪ኛ፦ለአቶ ስለሺነህ በቅድሚያ ስለሰጠህኝ አስተያዬት እግዚአብሔር ያክብርልኝ፡፡ ሆኖም የተፈጠሩት የስርዓተ ነጥብ ችግሮች እኔ ስርዓተ ነጥብ አስተማሪዎቼ ያላስተማሩኝ በመሆኑ አይደለም፡፡ ባይገርምህ ሙያዬ በራሷ ከጽሕፈት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ነገርግን በኮምፒውተርህ ወይም የፕሮግም ችግር ሊሆን ይገባል፡፡ እንኳን እኔ አንድ የKG ተማሪ ስርዓተ ነጥብ እንዴት መጠቀም እንዳለበት የሚያውቅ ይመስለኛል፡፡ አንተ ለእኔ ከላከው መልዕክት እንኳ በእያንዳንዱ ቃላት መካከል ሁለት ነጥብ ነጥላ ሰረዝ አለ ታዲያ ይህ የእኔ ስርዓተ ነጥብ አለማወቅ ይሆን? ጥያቄውን ለአንተው እተዋለሁ፡፡ ለማንኛውም አመሰግናለሁ። ሠላም ሁንልኝ።

የአብዛኞ፟ች፡ጸሐፊዎችን፡ሥርዓተ፡ነጥብ፡አጠ፟ቃቀም፡ሲ.ገ፟ነዘበው፤የእንግልጣሩን፡ፊደል፡ ሥርዓተ፡ነጥብ፡አጻጻፍ፡ይከ፟ተላሉ።እንዴት፡ቢ.ባል፦ ፩ኛ-___,=፣ ፪ኛ- ;=፤ ፫ኛ- .=። እን ግዲህ፡ንጹሕ፡ኢትዮጵያኖቹ፡እኛ፡የቃላት፡ድንበር፡አካ፟ላይዎቹን፡ብቻ፡ላለመጠ፟ቀም፡ታቅ፟ደ። ለምን!?።የእንግልጣሩ፡ፊደል፡(፡)፡ስለሌሉ፟ት፡የእኛውም፡አይኑረው፡ማለታቸው፡ይሆን?።

ስለዚ.ህ፤ሥነ፡ነጥበ፡ሥርዓቱን፡በተመለከ፟ተ፡ከቡር፡ንቡረ፡እድ፡ኤርምያስ፡ከበ፟ደ፡ወልደ፡ ኢ፟የሱስ፡ካልባረ፟ኩት፡ዘወር፡ብሎ፡ሊ.ያው፡የእሚ፟ችል፡እንደ፡ሌለ፟፡ስለ፡ተገነ፟ዘበ፡ግዜ፡አብቃቅተው፡ እንዲቸገ፟ሩበ፟ት፡ስለሺ.ነህ፡ትሕትኛ፡በተሞላበ፟ት፡ቅንነ፟ት፡ከል፟ብ፡ይማ፟ጸናል።

የኢትዮጵያኛ፡ፊደሎቻችንን፡በእንግልጣሩ፡አነ፟ባበብ፡የጻፈውን፡እንዲመ፟ለከ፟ቱለት፡ ልኮል፟ዎት፡ነበ፟ረ።እኛ፡አስፈላ፟ጊ፡ስላልመሰ፟ለዎት፡ይሆን?፡መልስ፡ያልሰጡት።ግዜ፡ሲ.ያገኙ፡ አስተያየትዎን፡ብገልጹለ፟ት፡የእሚ፟ያመሰግን፡መሆኑን፡ይገልጻል፟።በተረ፟ፈ፡ደህና፡እንሁን።

ሀገሩን፡አርግዞ፡የእሚ፟ወልድ፡ቢ.ኖር፣
የመጀ፟መ፟ሪያው፡ሰው፡እኔው፡እሆን፡ነበ፟ር።

፫) ግዜ፡እሚኖርዎት፡ከሆነ፡እባክዎ፡የእሚከተለውን፡በማር፡የተለወሰ፡ እሬት፡ዓይነት፡አጻጻፍ፡ያርርሙልን።

ውድ ስለሺነህ፣

ለመልስ ምት ጽሁፍህ እና ምክርህ እጅግ አድርጌ አመሰግንሃለሁ፡፡ የጽሁፍህ ይዘትና መደምደሚያ ለእኔ እንደገባኝ በጥናት ላይ ያልተመሰረተ ጽሁፍ መፃፌ ትውልድ የሚያጠፋ ስህተት መሆኑን ልትነግረኝ ፈልገሃል፡፡ ይሁን እንጂ የጽሁፌን መንፈስ አጣጥመህ የተረዳህ አልመሰለኝም፡፡ ምክንያቱም በጽሁፉ ውስጥ አማርኛ ቋንቋ እንደማንኛውም ቋነቋ ሙሉ መሆኑ ተገልፆ፤ ፊደላቱም የአፍሪካ ብቸኛ ኩራት መሆናቸው ተነግሯል፡፡ ይሁን እንጂ የአማርኛ ጽሁፍ የሚወለጋገድባቸው ወጣቶች መብዛታቸው የአደባባይ ምስጢር ነውና ምን ይሆን መንስኤው ለሚለው መልስ ለመስጠት እንደ ‹አማርኛ አፍቃሪነቴ› የተውተረተርኩበት ጽሁፍ ነው፡፡ በጽሁፉ ላይ ለመንስኤዎቹ ‹መደዴ› ብዬ የጠቀስኳቸውን መላ ምቶች ያስቀመጥኩ ቢሆንም ‹መደዴ› የሚለው ቃል እንደው ለትህትና ይሁነኝ ብዬ ያደረግኩት እንጂ ለነገሩስ በጣም ለረዥም ጊዜ ሳሰላስል እና መላምቴን ስህተት የሚያደርጉ እውነታዎች ያሉ እንደሁ ሳፈላልግ ቆይቼ ነበር፡፡ ለምሳሌ በፊደል ገበታችን ላይ የ‹ሀ› እና ‹አ› ግዕዝ እና ራብዕ ድምፆች ተመሳሳይነት በፊደሉ ፈጣሪ አባቶቻችን ስህተት እንዳልተፈጠረ የሚነግረኝ ተመራማሪ እንደማይመጣ በሙሉ ልብ እወራረዳለሁ፡፡እኔ በአማርኛ ጽሁፍ እና አጻጻፍ ዘይቤ በፍቅር ወድቄያለሁ፡፡ ቋንቋ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታልም እንዲሉ አማርኛም በዘመኑ ብዙ ጥቃቅንና ግዙፍ ለውጦችን እያስተናገደ እዚህ መድረሱ አይካድም፡፡ በጉልህ ብንመለከተው እንኳን የአባቶቻችን አባቶች አማርኛን ፈጥረውታል፣ አባቶቻችን ፊደል ሰጥተውታል፣ እኛ ደግሞ ፊደላቱ ላይ የምናገኛቸው ግድፈቶችን አርመን ለልጆቻችን ብናስተላልፈው ምንድን ነው ችግሩ? ዓለም ጎዶሎ እንደመሆኗ ሁሉም ስራዎች ሙሉ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ እንደመታደል ሁኖ ግን ዓለም ለውጥ ላይ ናት፡፡ ለውጥ አማጪዎችም እኛ በመሆናችን ዓለማችንን ስትለወጥ ማየት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ አማርኛችን ላይ ያሉትን ድክመቶች በማረም፡፡በነገራችን ላይ ክቡር ዶ/ር ሐዲስ አለማየሁ የሚጠብቁ ፊደላት አናት ላይ ዘማሪ ዳዊት ከተጠቀመባቸው 10 የዜማ ምልክቶች መካከል ይዘት የተሰኘውን ትዕምርት በማስቀመጥ እንዲለዩ በድንቅ ስራቸው ‹ፍቅር እስከ መቃብር› የጠቆሙትም በኔው ዓይነት አጻጻፉ ላይ እንዲሻሻሉ የሚጓጉላቸውን ስርዓቶችን እያመለከቱ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በተረፈ ተቆርቋሪነትን ከልብ አደንቃለሁ፡፡ እኔም አንተም የምንጮኸው ለአንድ አላማ - ለአማርኛ ትንሣኤ ብሎም ልዕልና ነውና።befeqe@yahoo.com

**፬) በዬ፡ግዜው፡የጎዋ፡ሰሌዳችሁን፡በመጎብኜት፡እማርበታለሁ።እናም፡እግዚአብሔር ያሰንብትልኝ።ግዜ፡ሲኖረኝ፡በሰፊው፡እጽፍልዎታለሁ።**

**፭)** በላኩልኝም፡መልእክት፡ከልብ፡አመስግኛለሁ።በግልም፡ሆነ፡በኅብረት፡ጸሎት፡ስለ፡እምታስቡኝ፡ እግዚአብሔር፡ያክብርልኝ።በሰፊው፡ተንትኜ፡ለመጻፍ፡የአንድ፡መጽሐፍ፡ያህል፡ይሆናል።እንጂ፡ሀገሬን፡ (ሀገራችንን)፡ከሕይወቴ፡የበለጠ፡የእማስባት፡ይመስለኛል።ለጃንሆይ፡አገዛዝ፡ለኃ፡ወጣት፡ስለ፡ነበርኩ፣ በቀላሉ፡እንደዚያ፡ተደርምሶ፤እንደዚህ፡አስከፊ፡ሁኔታ፡ይመጣል፡የእሚል፡ግምት፡አልነበረኝም።ሁኔታው፡ ተፋጥኖ፡አገራችንን፡ለማገልገል፡በማንችልበት፡አቋም፣በዓለማት፡ተበትነን፡ለባርነት፡መጋለጣችን፡ ያሳዝነኛል።ታሪካችንንም፡ቀናተኞች፡ሲያበላሹት፡እያዩ፡ዝም፡ብለው፡ለምዕራባውያን፡የእሚሰግዱት፤ ቅብጣዊ፣ግሪካዊ፣ዕብራይስጣዊ፣.....ወዘተ፡ሊቀ፡ምሁር፡ነን፡የእሚሉት፡እና፡እርስዎ፡ደከመው፡ያዘጋጁትን፡ ሰፋድል፡እየተረጎሙ፡የእሚዘባነኑትን፡ሳይ፡ኢትዮጵያውያን፡መሆናቸውን፡እጠራጠራለሁ።አዕምሮየ፡ በሥነ፡መንግሥታዊ፡አመለካከት፡በስሎ፡ለሀገር፡እና፡ወገን፡ለማሰብ፡የእሚያስችለኝ፣በኢትዮጵያ፡ሀገራችን፡ በእኛ፡ዕድሜ፡የተካሄዱትን፡መንግሥታት፡አላውቃቸውም።ማለትም፡ተሳትፎ፡አላደረግሁባቸውም።ምን፡ ግዜም፡እግዚአብሔር፡ከክፉ፡ስለ፡እሚሰውረኝ፣ዐሥራ፡ሁለተኛን፡በተፈሪ፡መኰንን፡የማታ፡ትምህርት፡ ቤት፡ፈጽሜ፡በ፲፱፻፷፩፡ዓመተ፡ምሕረት፡ወጣሁ።በ፲፱፻፷፪፡አደገኛው፡ለውጥ፡ተደረገ።ከዚያ፡በኋላ፡ የሆነውን፡እልቂት፣ዝም፡ነው።

በአጭሩ፡ይኸን፡ልገልጽልዎት፡የሞከርኩት፣ከዚያ፡ግዜ፡ጀምሮ፡ኢዮብ፡ትዝ፡ብሎኝ፥“እግዚአብሔር፡ሰጠ፣ እግዚአብሔር፡ነሣ፡የእግዚአብሔር፡ስም፡የተባረከ፡ይሁን”፡እንዳለው፤እንደዚያ፡ልንደፈር፡የቻልነው፡ የሀገራችን፡ክብር፡በመነካቱ፡ነው፡ብየ፡አሰብኩ።እናም፣የተቻለኝን፡ያህል፡የሀገሬን፡ባህል፣ቋንቋ፣ታሪክ፣ ሊቀ፡ምሁራን፡ልጆቿን፡ከማሰብ፡እንዳልቆጠብ፡ሆኛለሁ።

ኑሮኝ፡ምን፡ለመሆን፡በማለት፡መሥዋዕትነቴን፡ለሀገሬ፡አስረክቤ፡አለሁ።

ኢትዮጵያችንን፡የአዲሱ፡ዓለም፡ሥርዓት፡ቢጋሯን፡እያሰላሸው፡ነው።ንጉሥ፡ጀምስ፡በእሚል፡ስም፡ የእሚታወቀው፡የእንግልጣሩ፡መጽሐፍ፡ቅዱስም፡ኢትዮጵያን፡በኩሽ፡እየቀየረ፡ወጣቱን፡ትውልድ፡ግራ፡ ለማጋባት፡ተነስቷል።ምን፡እንደ፡እሚሻለን፡ዐዋቂው፡ኃያሉ፡እግዚአብሔር፡ብቻ፡ነው።

እስተ፡አሁን፡ባህላችንን፡እንደ፡እሚወዱት፡በማሰብ፡ዝም፡አልኩዎት፡እንጂ፣አንተ፡እንዲሉኝ፡ልጽፍልዎ፡ ካሰብኩ፡ቆይቻለሁ።እና፣ከአሁን፡በኋላ፡አንተ፡እንዲሉኝ፡አደራዩ፡የጠበቀ፡ነው።

---

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ: ከንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ: ለእነዚህ የአቶ ስለሺነህ እ-ጦማሮች የተሰጠ መልስ፡-

**ይድረስ፡- ለኢትዮጵያዊው ወገኔ፡ አቶ ስለሺነህ።**

**በቅርቡ፡ እያከታተልህ የጻፍህልኝን፡ እ-ጦማሮችህን አግኝቼ ተመልክቻቸዋለሁ፤ እግዜር ይስጥልኝ! በውስጣቸው የገለጽሃቸውን አሳቦችህንና የሠነዘርሃቸውን አስተያየቶችህን፡ አድንቄአለሁ፤ ከእነዚህም መካከል፡ አንዱ፡ ዕድሜህን በመገመት፡ “አንቱታው” ቀርቶ፡ “አንተታውን” የመረጥህበት ሲኾን፡ ይህንኑ አጠራር፡ ደስ ብሎህ እንደምትቀበለው ስላስታወቅኸኝ፣ እኔም፡ ከትሕትናህ ጋር፡ ይህንኑ ፍላጎትህን በማጽናት መፈጸሜን፡ ይኸው ትመለከተዋለህ።**

**ይህን፡ በዚህ ቃል አቁሜ፡ የጥያቄዎችህን መልሶች፡ እንደሚከተለው አቅርቤልሃለሁ፡-**

**፩. ጥቁር ክርን ስለማሰር፡ ከአንዷት እመቤት ቀርቦ የነበረውን ጥያቄና ለዚያ ጥያቄ፡ እኔ የሰጠሁትን መልስ የያዘውን መዝገብ፡ አውጥቼ ለመመልከትና ለመመርመር አልሞከርሁም፤ ጥያቄህም፡ “ሙሉ በሙሉ ግልጽ ኾኖልኝ፡ በትክክል ገብቶኛል!” ለማለትም አልደፍርም። ይኹን እንጂ፡ አጥጋቢ መልስ ኾኖህ፡ “ምናልባት፡ የተምታታብህን ነገር አጥርቶና አስረድቶ ይፈታልህ ይኾናል! ካላረካህ ግን፡ ጥያቄህን አብራርተህ ስትልክልኝ፡ በዚያን ጊዜ ደግሞ፡ በበለጠ አፍታታልሃለሁ!” ብዬ በማሰብ፡ የሚከተለውን ምላሽ ሰድጄልሃለሁ፡-**

በቅድሚያ፡ ከዚህ ርእስ ነገር ጋር በተያያዘ፡ ለኀዘን፡ ነጭ፥ ወይም ጥቁር ልብስን ስለመልበስ፡ በመጽሐፎቹ ውስጥ የተገለጸው ፍሬ ነገር፡ ተጨምቆ ሲገለጽ፡ እንዲህ የሚለውን መልእክት ያዘለና ያስተላለፈ ኾኖ ይገኛል፦ "እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያን፡ የመጀመሪያው ትንሣኤ ሕይወት ባለዕድሎች ስለኾንን፡ 'የትንሣኤ ብርሃን ልጆች!' ነንና፡ ከደስታ በስተቀር፡ ኀዘን የለብንም። በሠርግ፥ ወይም፡ የደስታ በዓሎቻችንን በምናከብርባቸው ጊዜያት ብቻ ሳይኾን፡ ሕያዋን ወገኖቻችን፡ ከመካከላችን፡ በሥጋ ዕረፍት ሲያንቀላፉ፥ ነጭ ልብስን ለብሰን፡ በሓሤት ተመልተን የምንሸኛቸው፡ በዚህ ምክንያት ነው። ጌታ፡ **'ሙታናቸውን ይቀብሩ ዘንድ፡ ሙታንን ተዉዋቸው!'** ያላቸው፡ ሌሎች፡ "ክርስቲያኖች ነን" ባዮች ግን፡ የሞቱ ወገኖቻቸውን፡ ጥቁር ልብስን ለብሰውና መራራ የኀዘን ልቅሶን በማድረግ ሲቀብሩዋቸው እናያለን።"

በዚህ ሃይማኖታዊ መሠረት ላይ የታነጸውን፡ ማለትም፡ የሥጋዊ ሞት ኀዘንን፡ ወደትንሣኤ ሕይወት ደስታ የለወጠውን፡ ይህን መለኮታዊ ሥርዓታችንን፡ ያቃወሰውን ባዕድ ልማድ፡ የግብፅ Orthodox ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፡ ወደአገራችን ገብተው፡ በሙታን ቀብር ጊዜ፡ ልቅሶ እንዲለቀስና ለመራራው ኀዘን፡ ጥቁር ልብስ እንዲለበስ የሚያደርገው ባህል እንዲጠናከር በማድረጋቸው፡ እነሆ፡ እስካኹን ድረስ፡ እውነተኛው የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሥርዓታችን ተግዞና ባዕዱ ልማድ ሠልጥኖ ይታያል።

የእኔ ቤተሰብ፡ በበኵር ልጃችን ዕረፍት ጊዜ፡ የተዋሕዶ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓት ተከትለን፡ ኹላችንም፡ ነጭ ያገር ልብስን በመልበስ፡ ያካኼድነው ጸሎት፡ በዚህ አንጻር፡ ማኅሌትንና ቅዳሴን የተመላ፡ የደስታና የምስጋና እንጂ፡ የኀዘንና የለቅሶ አልነበረም።

ከጥቁር ክር ጋር ስለተያያዘው ማተብ የተሠነዘረው ትችት ደግሞ፡ እንዲህ በሚል ቃል ሊጠቃለል ይቻላል፦ "እኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በክርስትና ጥምቀታችን ጊዜ፡ በየአንገታችን ሊታሠርልን የሚያስፈልገው፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር፡ በቃል ኪዳን የተቀበልነውና የሰንደቅ ዓላማችንን ቀለማትን አዋሕዶ የያዘው፡ አረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ክር ማተብ ሊኾን ይገባል። ዳሩ ግን፡ እነዚሁ ግብፃውያን፡ ያን፡ መለኮታዊ ሕያው ቅርሳችንን፡ በእነርሱ፡ የባዕድ አምልኮ አረማዊነት ምልክታቸው ለውጠውት ይገኛል፤ ይኸውም፡ እነርሱ፡ እስከዛሬ እየሠሩበት ባለውና ነጭ፥ ጥቁርና ቀይ በኾነው፡ በግብፃውያን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማቸው ቀለማት መተካታቸው ነው።፡

የእግዚአብሔር የኾነውን ሥራ ለማፍረስ የደፈረው፡ ይህ የግብፃውያን ድርጊት፡ ሰይጣናዊ በመኾኑ፥ ጥቁር ክርን፡ ማተብ የማድረጉም ልማድ፡ ወደኢትዮጵያ ገብቶ፡ በኢትዮጵያውያን ላይ የሰፈነው፡ ከዚሁ የተነሣ በመኾኑ፡ ይኸው፡ የግብፃውያን ታላቅ ኃጢአት የኾነው ግብር፡ "ስለጥቁር ክር፥ ወይም፡ ማተብ፡ ለእመቤቷ በተሰጠው መልስ፡ የዲያብሎሳዊ መንፈስ ርኩስ አምልኮነትን ይገልጻል!" አስሰኝቷል።

፪. ሥርዓተ ነቍጣችንን (ነጥባችንን) የሚመለከተው ርእሰ ነገር፡ ከመጀመሪያው ትኵረትን የሰጠህበት ዋና ቍም ነገር መኾኑን አውቀዋለሁ፤ በዚህም ጉዳይ ላይ፡ በቀጥታና አልፎ አልፎ፥ በየአጋጣሚውም፡ ተወያይተንበታል። አኹንም፡ እግዚአብሔር፡ ለኢትዮጵያ፡ የወሰነው ቀን ደርሶ፡ ፈቃዱ እስኪፈጸም፣ ማለትም፡ በሥነ ጽሑፋችን ረገድ ያለው፡ የነጥባችን ሥርዓት፡ በመንፈስ ቅዱስ አንድነትና ስምምነት፡ ብሔራዊና መንግሥታዊ ውሳኔ እስኪስሰጠው ድረስ፡ እስካኹን፡ በተያዘው መልክ፡ ውይይቱን፡ በቅንነትና በታማኝነት መቀጠሉ ይጠቅማል። የአቶ በፈቃዱ ኃይሉንም፡ "በማር የተለወሰ፡ እሬት ዓይነት አጻጻፍ"፡ በዚሁ፡ የውይይት አዎንታዊ ገጽታው ተቀብለህ አመዛዝነው!

በእኔ በኩል የማደርገው ጥረት፡ ከፊደላችን አሌፋትና ሆህያት ጀምሮ ያለው ኢትዮጵያዊው የሥነ ልሳንና የሥነ ጽሑፍ ሥርዓታችን ቅርስ እንዲጠበቅ ለማድረግ መኾኑን፡ በሚበቃ የተገነዘብኸው መኾኑን ከአጻጻፍህ ከተረዳሁት ቆይቻለሁ። ምንም እንኳ፡ እስካኹን ባለመታተሙ ምክንያት፡ ለሥርጭት በቅቶ፡ ከሕዝብ እጅ ባይደርስም፡ በደርግ እሥር ቤት በነበርሁበት ጊዜ ባዘጋጀሁት፡ "አዳም እና ሔዋን፡ በኢትዮጵያ!" በሚለው፡ በባለሦስት ጥራዝ መጽሓፌ መቅድም ውስጥ፡ በተለይ የማጥበቅና የማላላት መፍትሔያዊ ሥርዓት ሊደረግላቸው ስለሚያስፈልጉ ቃሎቻችን፡ የሠነዘርሁት አስተያየት እንዳለ፡ አመልክቼህ የነበረውንም ቁም ነገር ታስታውሰዋለህ።

በአንተም በኩል፡ ለዚህ፡ ለቃላት መጥበቅና መላላት ችግር፡ "መፍትሔ ይኾናል!" ብለህ ያቀረብኸው ዘዴ፡ እርሱም፡ በሚጠብቀው ሆሄ ዐናት ላይ፡ ነቁጥን፥ ወይም፡ ሠረዝን በመለዋወጥ እያደረግህ የምታሳየው ሙከራ፡ የቋንቋችን ሥነ ጽሑፍ ሊሻሻል የሚገባው በመኾኑ ነውና፡ ይህ ጥረትህ፡ እንደሚያስሞግስህ አይጠረጠርም።

ለዚህ ችግር፡ መደበኛና ቀዳሚ የኾነ መፍትሔ እንዳለው ይታወቃል፤ ያም መፍትሔ፡ አንድ ቃል፡ ለምሳሌ፡ "ይገባል" የሚለው ቃል፡ ላልቶና ጠብቆ ሲነገር፡ የሚሰጠው ትርጉም፡ የተለያየ በሚኾንበት ጊዜ፡ ይህን ልዩነት ለማሳየት፡ መግለጫ ምልክት ሊኖር እንደሚገባ እሙን ነው፤ ይህም፡ ሌላው ማማረጫ መፍትሔ ኾኖ፡ በአንተ ዘንድ፡ እየተሠራበት ያለው ዘዴ ነው፤ በዚህ ዘዴ መሠረት፡ በሚጠብቀው ሆሄ፡ ማለትም፡ በ"ገ" እና በ"ባ" ዐናት ላይ፡ የነጥብ፥ ወይም፡ የሠረዝ ምልክት ይደረግበታል፤ ምልክቱ ሳይደረግበት፡ እንዲሁ፡ ሌጣ ኾኖ በሚተውበት ጊዜ ግን፡ "ላልቶ ይነበብ!" ማለት ሲኾን፥ ጠብቆ እንዲነበብ ሲያስፈልግ ግን፡ እንደሥርዓተ ጽሑፉንና ንባባችን መርሖ፡ መጻፍ ያለበት፡ "ይግገብባል" ተብሎ ነው፤ "መደበኛና ቀዳሚ የኾነው መፍትሔ" የተባለውም፡ ይህ ነው።

እንግዴህ፡ ከእነዚህ ከኹለቱ፥ ወይም፡ ሌላም ቢኖር፡ ከሚቀርቡት ማማረጫ መፍትሔዎች መካከል፡ "ይኼኛው ይኹን!" ብሎ የመወሰኑና የመበየኑ ፋንታ፡ የዚያ፡ የኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት "የቋንቋ ባለሥልጣን አካል" መብት ይኾናል። ይህ አካል፡ ዛሬም ቢኾን፡ በዚሁ አገልግሎታችን አማካይነት፡ አገልግሎቱን በማበርከት ላይ ስለኾነ፡ ተስማምተን የምንሰጠው ውሳኔ ሲኖር፥ ያንኑም፡

ኹላችንም የምንቀበለው ሲኾን፡ ያን፡ የተወሰነና የተበየነ ሥርዓት፡ የመቀመሪያ ባለሙያዎቻችን ጭምር፡ በተግባር ላይ የሚያውሉት ይኾናል።

እንደዚሁ ኹሉ፡ የነጥባችንም ሥርዓት፡ በዚሁ መልክ፡ ሊታይና መፍትሔ ሊደረግለት አያዳግትም፤ ይህን እውነታ፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል መግለጽ ይቻላል፡- ጥንቱኑም ቢኾን፡ በሥነ ጽሑፋችን ሥርዓት ውስጥ፡ የኹለቱ ነጥብ ያስፈለገው፡ በእጅ ሲጻፍ፡ አንዱን ቃል ከተከታዩ ለመለየት፡ በግድ አንድ ዘዴ መኖር ስላለበት መኾኑ አያጠያይቅም።

ምክንያቱ ይህ ከኾነ፡ ታዲያ፡ ለቃላት መጥበቅ፡ ከላይ የተጠቀሰው፡ መደበኛው የአሌፋቱ መደራረብ፡ ማለትም፡ "ይግገብባል" መባሉ ቀርቶ፡ ነጥቡ፥ ወይም፡ ሠረዙ፡ "የተሻለ መፍትሔ ይኾናል!" እንደተባለው ኹሉ፡ በቃላቱ መካከል፡ የሚከተበውን፡ ኹለት ነጥብ በማስቀረት፡ የተለካና የተካከለ መለያ እያደረገ በሚያቀላጥፈውና አውቆ ከዋኝ በኾነው፡ በዘመናዊው መጻፊያ፥ ወይም፡ መቀመሪያ፡ በሚሰጠው ባዶ ቦታ በመተካት መጠቀሙ፡ የሚበጅና የሚሻል መኾኑ ግልጽ ነው።

ይህም ሲኾን፡ አኹን እኔ፡ በዚህና በሌሎቹ ጽሑፎቼ እየሠራሁበት እንደሚታየው፡ በኹለት ነጥቡ የመጠቀሙን ዘዴ በተሻለ መልክ መቀጠል ይቻላል፤ ይኸውም፡ በንዑስ ሠረዝ (፣ እና ፥)፥ ከዚያም፡ በድርብ ሠረዝ (፤)፥ በመጨረሻም፡ በአራት ነጥብ (።) ተከውነውና ተሰልፈው ላሉት፡ ለአንድ ሙሉ የዐረፍተ ነገር ቃላት፥ ኹለቱን ነጥብ፡ የንባብ እና የጽሑፍ እፎይታ፥ ወይም፡ ቆይታ፡ መግቻ አድርጎ እንዲያገለግል ማስቻሉ ነው።

በዚህ ረገድ፡ አንተም በማነጻጸር እንዳቀረብኸው፡ የእኛ፡ ኢትዮጵያኛው የነጥብ ሥርዓት፡ ከእንግሊዝኛውም ይልቅ የተሻለና የበለጠ ኾኖ መገኘቱን፡ በቀላሉ ማመልከቱና ማረጋገጡ አዳጋች አይኾንም፤ ይህም ማለት፡ በኹለት ዓይነት ምልክት የተከተበው፡ የእኛ "፣" እና "፥" ንዑስ ሠረዝ፡ የእነርሱን "," comma፥ የእኛ "፤" ድርብ ሠረዝ፡ የእነርሱን፡ ";" semi-colon፥ የእኛ "።" አራት ነጥብ፡ የእነርሱን፡ "." Full stop ከተካ፡ ከላይ ለተጠቀሰው፡ የጽሑፍና የንባብ ማሳረፊያ፥ ወይም፡ መግቻ የተጠቀምንበትን፡ የእኛን "፡" ኹለት ነጥብ የሚተካ፡ ሌላ ነጥብ፡ እነርሱ የላቸውም ማለት ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ፡ እዚህ ላይ ሊወሳ የሚገባው ተመሳሳይ ቁም ነገር አለ፤ ይኸም፡ ለምሳሌ፡ እኔ፡ "እንደኾነ" ብዬ፡ አያይዤና አንድ አድርጌ የምጽፈውን ቃል፡ "እንደ - ኾነ" በሚል መልክ፡ ለያይቶ የሚያቀርበው የአጻጻፋችን ባህል ነው። ታዲያ! "እንደ - እዚህ ከ - ኾነ፡ ለ - ምን፡ ይኸው አጻጻፋችን፡ እስከ - ዛሬ በ - እነዚህ እና እነዚህን በ - መሰሉት ቃላት ላይ ሳይጸና ቆየ? በ - ቃላቱ ላይ የሚ-ቀጸሉት፥ ወይም፡ የሚ-ታዘሉት የ - አገባብ ዘሮች፡ ከ - እነዚህ ቃላት ተለይተው እንዲ - ጻፉ ስለ - ምን የተ-ገባ ኾነ? ሥርዓቱ፡ ስለ - ምን፡ በ - እዚህ ዓይነት ሊዘበራረቅ ቻለ? ስለ - እዚህ፡ ይህም ችግር፡ መፍትሔ ሊ-ፈለግለት ይገባል።"

በእኔ በኩል፡ ለዚህ ዝብርቅርቅ አጻጻፍ፡ ያገኘሁት ማስተካከያ፡ ከላይ ተለያይቶና ተዛንቆ የተጻፈውን ዐረፍተ ነገር፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ እንዲህ፡ በአንድ መልክ፡ አያይዞ እንዲጻፍ ማድረጉ ነው፡-

"እንደዚህ ከኾነ፡ ለምን፡ ይኸው አጻጻፋችን፡ በእነ "እንደ፥ ከ፥ ለ፥ እስከ፥ በ፥ የሚ፥ እንዲ" እና "ስለ" በተባሉት፡ በእነዚህና እነዚህን በመሰሉት ቃላት ላይ አልጸናም? በቃላቱ ላይ የሚቀጸሉት፥ ወይም፡ የሚታዘሉት የአገባብ ዘሮች፡ ከእነዚህ ቃላት ተለይተው እንዲጻፉ ስለምን የተገባ ኾነ? ሥርዓቱ፡ ስለምን፡ በእዚህ ዓይነት ሊዘበራረቅ ቻለ? ስለዚህ፡ ይህም ችግር፡ መፍትሔ ሊፈለግለት ይገባል።"

፫. ተመልከቼ፡ አስተያየቴን እንድሰጥህ፡ በእንግልጣሩ አነባበብ "ጽፌ፡ ልኬልዎት ነበር!" ያልከኝ፡ የኢትዮጵያኛ ፊደሎቻችን፡ ሳይደርሱኝ ቀርተው ይኹን፥ ወይም፡ በሌላ ምክንያት፡ በመቀመሪያዬ ውስጥ ስላላገኘሁት፡ ቅጂውን ልከህልኝ፡ ለጥያቄህ፡ አስፈላጊውን መልስ ብሰጥህ ደስ ይለኛል።

"ሀገሩን አርግዞ የሚወልድ ቢኖር፤ የመጀመሪያው ሰው፡ እኔ እኾን ነበር!" የሚለው ግጥምህ፡ ኢትዮጵያዊ ማንነትህን አረጋግጦ የሚያሳይ ስለኾነ፡ እግዚአብሔር፡ ለኢትዮጵያ የመደበው "ቀኑ" እስኪደርስ፡ ትዕግሥቱንና ጽናቱን እንደሚያድለን በማመን እጸልያለሁ። በዚህ ረገድ፡ በግልም ኾነ፥ በማኅበር ጸሎታችን ላይ የምናደርገውን የተዘክሮ ስም አጠራርህን ለማስተካከል ይረዳን ዘንድ፡ የቃል ኪዳን ምስክርነቱን ሥርዓት ፈጽመህ፡ የሰንደቅ ዓላማችንን (አረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ፡ ቀለማት) ማተብ፡ በአንገትህ ያሠርህ መኾንህን ብታሳውቀኝ ደስ ይለኛል።

---

## ከአቶ ስለሺነህ የደረሰን ኹለተኛው እ-ጦማር።

ለጥያቄው፡መልስ፡ስለ፡ላኩልኝ፡ [ስለሺነህ] ከልብ፡እጅ፡መሰገንዎት፡ነው።

በ፡ደብዳቤዎ፡ውስጥ፡....."ዕድሜህን፡በ፡መገመት፡"አንቱ፡ታው"፡ቀርቶ፡"አንተ፡ታውን" የ፡መረጥህበት፡......"፡በ፡ማለት፡የ፡ጀመሩትን፡መሠረተ፡ሐሣብ፡አስተላልፎት፡የነበረው፡መልእክት፡ዕድሜውን፡በ፡መገመት፡መነሻ፡አልነበረም።የ፡ዋና፡ዓላማው፡ትኩረት፤እርስዎ፡ሥልጣኑ፡እ ና፡በ፡ተግባርም፡ለ፡ኢትዮጵያችን፡እና፡ሕዝቦቿ፡የፈጸሙትንም፡ሆኑ፡እዬ፡ፈጸሙ፡ስለ፡አሚጎኑት፤የ፡እርስዎ፡እርስዎታ፡ስለ፡ከበደው፡ነበረ።እናም፤ፍላጎቱን፡ስለ፡አሟሉለት፡እግዚአብሔር፡ያክብርልኝ፡ይላል።ዕድሜ፡ካነሱ፡ዘንድ፤ስለሺነህ፡የ፡ተወለደው፡በ፡፲፱፻፴፮፡ዓመተ፡ምሕረት፡ነው።

ስለ፡ማተብ፡ያስረዱትንም፡ተረድቶዎታል።በተለምዶ፡ማተብ፡በ፡መሳል፡ሲ፡ሰማ፡ያደገው፡እርስዎ፡ከ፡ገለጹለት፡ለ፡ዬት፡ባለ፡ሁኔታ፡የ፡እራሱ፡ግንዛቤ፡እንጂ፡ትኩረት፡ሰጥቶ፡እና፡ጠይቆ፡የተረዳው፡አልነበረም።ግን፡ሰወች፡ማተብ፡የ፡አሚለውን፡ቃል፡ከ፡ቀለም፡ጋራ፡አገናዝበው፤ጥቁር፡ከብቶችን፡ማተብ፤ቀዮችን፡አደይ፤ነጭዎችን፡ሻሽ፤ጠይሞችን፡ከፈይ፤......"፡እያሉ፡ሲ፡ጠሯቸው፡እዬ፡ሰማ፡ስለ፡አደገ፡ግንዛቤው፡እንዲያ፡ነበረ።ክርስትና፡በ፡ተነሣበት፡ግዜም፡ለአቡነ፡ኤዎስጣቴዎስ፡ተሰጥቶ፡የ፡ታሠረለት፡ነጭ፡ይሁን፡ብጫ፡ክር፡ነበረ፡መሰል።ካደገም፡በኋላ፡የ፡እናቱ፡አባት፤አያቱ፤ቀኝ፡ጌታ፡አለ፡ተገኜ፡ሰማያዊውን፡ሐር፡ዝባድ፡እዬ፡ሠኙ፡ሲ፡ሰጧቸው፤እርሱ፡ማርዳ፡እና፡ዛጎል፡እዬ፡ሰካ፡በ፡አንገቱ፡ያድርግ፡ነበረ።ቀጠን፡ያለውን፡ሰማያዊ፡ክርም፡በእራቁት፡አንገቱ፡ይደረግለት፡

ነሰረ።ስለ፡እዚህ፤መሠረቱን፡ያስረገጠ፡ትምህርት፡ስላስተማሩት፡ከ፡አክብሮት፡ጋራ፡ልባዊ፡ ምስጋናውን፡በ፡መደጋገም፡ያቀርብልዎታል።እርስዎም፡እንደገለጹት፤”ኢትዮጵያውያን፡የ፡ መጀመሪያው፡ትንሣኤ፡ሕይወት፡ባለ፡ዕድሎች፡ስለ፡ሆንን፡‘የትንሣኤ፡ብርሃን፡ልጆች!’፡ነንና፤ ከደስታ፡በስተቀር፡ኀዘን፡የሌብንም።ወገኖቻቸውን፡ጥቁር፡ልብስን፡ለብሰውና፡መራራ፡የ፡ኀዘን፡ ልቅሶችን፡በማድረግ፡ሲቀብሩዋቸው፡እናያለን።”በዚህ፡ሃይማኖታዊ፡መሠረት፡ላይ፡የታነጸውን፡ ማለትም፡የሥጋዊ፡ሞት፡ኀዘንን፡ወደትንሣኤ፡ሕይወት፡ደስታ፡የለወጠውን፡ይህን፡መለኮታዊ፡ ሥርዓታችንን፡ያቃወሰውን፡ባዕድ፡ልማድ።፡የግብፅ፡”Orthodox”፡ቤተ፡ክርስቲያን፡መሪዎች፡ ወደ፡አገራችን፡ገብተው፡በሙታን፡ቀብር፡ጊዜ፡ልቅሶ፡እንዲለቀስ፡እና፡ለመራራው፡ኀዘን፡ጥቁር፡ ልብስ፡እንዲ፡ለበስ፡የ፡እሚያደርገው፡ባህል፡እንዲ፡ጠናከር፡በማድረጋቸው፡እነሆ!፡እስካሁን፡ድረስ፡ እውነተኛው፡የቅዱሱ፡ኪዳን፡ኢትዮጵያዊው፡ሥርዓታችን”ተግዞ፡እና፡ባዕዱ፡ልማድ፡ሠልጥኖ፡ ይታያል።.........አረንጓዴ፥ብጫና:ቀይ:ክር:ማተብ:ሊሆን፡ይገባል።ዳሩ፡ግን፡እነዚሁ ግብፃውያን፡ያን፡መለኮታዊ፡ሕያው፡ቅርሳችንን፡በእነርሱ፡የባዕድ፡አምልኮ፡አረማዊነት፡ ምልክታቸው፡ለውጠውት፡ይገኛል።ይኸውም፡እነርሱ፡እስከ፡ዛሬ፡እዬ፡ሠሩበት፡ባለውና፡ነጭ፥ ጥቁርና፡ቀይ፡በሆነው፡በግብፃውያን፡ብሔራዊ፡ሰንደቅ፡ዓላማቸው፡ቀለማት፡መተካታቸው፡ነው”።

የ፡እርስዎን፡አሳባል፡ስለሺ.ነህ፡መልሶ፡የ፡ጻፈሰት፡ምክንያት፤ግብፅ፡እና፡ግሪክ፡አገር፡ ለ፡ትእምርተ፡መለኮት፡ተልከን፡ተምረናል፡ባዮች፡ወገኖቻችን፡ያደረሱብንን፡በደላዊ፡ትዝብት፡ ለ፡መግለጽ፡ስለ፡አጋጠመው፡ነው።፡ለዚህም፡ምሣሌ፡አድርጎ፡ማቅረብ፡የ፡ፈለገው፡ሊቀ፡ምሁር፡ አምሣሉ፡አክሊሉ፡እና፡ሊቀ፡ምሁር፡ጌታቸው፡ኃይሌን፡ነው።ሁለቱም፡ፀረ፡ቤተ፡ክህነት፤ፀረ፡ የ፡ኢትዮጵያ፡ፊደሎች፡እና፡ፀረ፡የ፡ኢትዮጵያ፡ሥነ፡ሥርዓተ፡ጽሑፍ፡መሆናቸውን፡በጻፏቸው፡ ጽሑፎች፡አስፍረዋቸው፡በ፡ማግኘቱ፡ነው።

ለ፡ምሣሌ፡-፩ኛ፥ጌታቸው፡ኃይሌ፡በ፡አንድ፡መጽሓፋቸው፡ውስጥ፤”መቸም፡ሳይገርማችሁ፡ አይቀርም”።.......ብለው፡እኔ፡ግዕዙን፡የ፡ተማርኩት፡እንደ፡ሌሎቹ፡...........የ፡ቅኔ፡ባለሟሎች፡ ሊቃውንት፡በ፡ተማሩሰት፡ሥፍራ፡....አለ፡መሆኑን፡ገልጸው፤መቃብር፡ቤት፡እዬ፡ኖሩ፡በ፡አሳታቸው፡ እና፡በ፡ቅድስት፡ሥላሴ፡መንበረ፡ጸባዖት፡መንፈሳዊ፡መካነ፡ትምህርት፡ጀምረው፤በ፡ግብፅ፤ጀርመን፤ እስራኤል፤............በ፡መሳሸሉት፡መማራቸውን፡ያቸታሉ።፪ኛ፥አምሣሉ፡አክሊሉ፡የ፡አዲስ፡ አበባው፡መካነ፡አእምሮ፡የ፡ቋንቋ፡ክፍልን፡በሀላፊነት፡እዬ፡መሩ፡ወደ፡፲፭፡ሰወች፡ያህል፡ይዘው፡ የ፡ፊደሎቻችንን፡መቐነስ፡አግባብ፡ነው፡ብለው፡ስላሙኑሰት፡የ፡ሰጡት፡አስተያየት፡እጅግ፡አሳዛኝ፡ ሁኖ፡ታይቶታል።ሕዝብ፡ሳያውቀው፡በ፡፲፭፡ሰወች፡ስብሰብ፡ድምፅ፡ይሸጥሰት፡ብለው፡ወሸነው፡ ውድቅ፡ይሁኑ፡ብለው፡የፈረዱሳቸውን፡ፊደሎች፡ከ፡ገበታ፡እንዲነሡ፡ወሸኑ።ሌላው፡አስገራሚው፡ አሳባላቸው፡ደግሞ፤ደ፡እና፡ጸ፡ስለ፡እሚመሳሸሉ፡ጸን፡ከ፡ገበታው፡እንዲ፡ወጣ፡ማድረጋቸው፡ነሰረ። በ፡መቀጠልም፡ስለ፡ፊደሎች፡አቐናነስ፡ውሳኔ፡እንዲ፡ሰጥሰት፡ለ፡ደርግ፡ጽሕፈት፡ቤት፡ደብዳቤ፡ አስገብተው፡ውሳኔው፡ስለ፡ዘገዬ፤”ደርግ፡ቤተ፡ክህነትን፡ስለ፡እሚፈራ፡ነው፡በ፡እሚል፡ብቻቸውን፡ ወሸነው፡ሥራ፡መጀመራቸውን፡አብሥረዋል”።እንግዲህ፡እንዲህ፡አቐማጥላ፡ላሳደገች፡አገር፡እና፡ ግብር፡እዬ፡ከፈለ፡አስተምሮ፡ላሳደገ፡ሕዝብ፡ምን፡ወረታ፡ተከፈለለት?።

ከ፡እዚህ፡ላይ፤እንደ፡እነሱ፡ግብፅ፡አገር፡ከ፡ተማሩት፡አንዱን፡ሀገር፡ወዳድ፡ኢትዮጵያዊ፡ መጥቀስ፡ግድ፡ይለዋል።አቶ፡በትረ፡ጽድቅ፡ካሣ፡ከ፡ጥሊያን፡ወረራ፡በ፡ኋላ፤ዘመናዊው፡እና፡የ፡ቤተ፡ ክህነት፡ትምህርት፡አብሮ፡እንደ፡እንዲ፡ሄድ፡በ፡ማሥሠብ፡የ፡ቤተ፡ክህነት፡ምሁራንን፡በ፡ምክር፡ አሳምነው፡እና፡ተቀጥረው፡እንዲ፡አስተምሩ፡አድርገው፡ከፍ፡ያለ፡ውጤት፡አስገኝተዋል።በ፡አንድ፡ ዘመን፡ለ፡ከፍተኛ፡ትምህርት፡ውድድር፡ተደርጎ፤ከ፡ጎጃም፡፭፡ተማሪዎች፡አልፈው፡ከ፡ጎንደር፡ ምንም፡ስለ፡አላለፈ፥በ፡ጊዜው፡የ፡ነሰሩት፡የ፡ትምህርት፡እና፡ሥነ፡ጥበብ፡ምሉክ፡”ከ፡ጎጃም፡

በ፡ኢ.ትዮጵያውያን፡መምህራን፡ተምረው፡አምስት፡ተማሪዎች፡ሲያልፉ፤ከ፡ጎንደር፡ግን፡በ፡አመ
ሪካን፡መምህራን፡ተምረው፡አንድም፡አላለፈ.”፡ሲሉ፡ተናግረዋል።ያን፡ግዜ፡የ፡ጎጃም፡ትምህርት፡
ቤቶች፡አስተዳዳሪው፡አቶ፡በትረ፡ጽድቅ፡ካሣ፡ከ፡አስተዳደር፡ሥራቸውም፡በ፡ላይ፡ክፍል፡እዬ፡ገቡ፡
አስተምረዋል።ስለዚህ፣ጌታቸው፡እና፡አምሣሉን፡የ፡መሳሸሉትን፡ኢ.ትዮጵያ፡ትፋረዳቸዋለች።

ለዚህም፡ነው፥ስለሺ.ነህ፡ቋንቋውን፡እና፡ባሕሉን፡ፈረንጅ፡ሊ.፡አስተምረኝ፡አይችልም፡
የ፡እሚለው።ሠልጥነናል፡በ፡እሚሉት፡አገር፡ቋንቋቸውን፡አስተማሪ፡ሊ.፡ቀጥሩ፡ሲ.፡ፈልጉ፡የ፡ትውል
ድ፡ቋንቋውን፡ተናጋሪ፡እንፈልጋለን፡ብለው፡ማስታዎቂያ፡ያወጣሉ።ዛሬ፡ዛሬ፡ስደተኛው፡ስለ፡በዛ
ላቸው፡የ፡ስደተኛ፡ልጆችን፡እንድናስተምር፡ስለ፡ፈቀዱ፡ግራ፡ላጋባ፡አይገባም።

...............“ይግገብባል”፡መባሉ፡ቀርቶ፡ነጥቡ፥ወይም፡ሠረዙ፡“የተሻለ፡መፍትሔ፡
ይሆናል!”።እንደተባለው፡ሁሉ፡በቃላቱ፡መካከል፡የሚከተበውን፡ሁለት፡ነጥብ፡በማስቀረት፡የተ
ለካና፡የተካከለ፡መለያ፡እያደረገ፡በሚያቀላጥፈውና፡አውቆ፡ከዋኙ፡በሆነው፡በዘመናዊው፡መጻፊ
ያ፥ወይም፡መቀመሪያ፡በሚሰጠው፡ባዶ፡ቦታ፡በመተካት፡መጠቀሙ።የሚበጅና፡የሚሻል፡መሆኑ፡
ግልጽ፡ነው።ይህም፡ሲሆን፡አሁን፡እኔ፡በዚህና፡በሌሎቹ፡ጽሑፎቼ፡እየሠራሁበት፡እንደሚታየው፡
በሁለት፡ነጥቡ፡የመጠቀሙን፡ዘዴ፡በተሻለ፡መልክ፡መቀጠል፡ይቻላል፤ይኸውም፡በንዑስ፡ ሠረዝ(፣
እና፥)፥ከዚያም፡በድርብ፡ሠረዝ(፤)፥በመጨረሻም፡በአራት፡ነጥብ(።)ተከውነውና፡ተሰልፈው፡
ላሉት፡ለአንድ፡ሙሉ፡የዐረፍተ፡ነገር፡ቃላት፥ሁለቱን፡ነጥብ፡የንባብ፡እና፡የጽሑፍ፡ እፎይታ፥ወይም፡
ቆይታ፡መግቻ፡አድርጎ፡እንዲያገለግል፡ማስቻሉ፡ነው።በዚህ፡ረገድ፡አንተም፡በማነጻጸር፡
እንዳቀረብ፡ኸው፡የእኛ፡ኢ.ትዮጵያኛው፡የነጥብ፡ሥርዓት፡፡ከእንግሊ.ዝኛውም፡ይልቅ፡የተሻለና፡
የበለጠ፡ሆኖ፡መገኘቱን፡በቀላሉ፡ማመልከቱና፡ማረጋገጡ፡አዳጋች፡አይሆንም፤ይህም፡ማለት፡
በሁለት፡ዓይነት፡ምልክት፡የተከተበው፡የእኛ“፣”እና“፥”ንዑስ፡ሠረዝ፡የእነርሱን፡“,”comma፥
የእኛ“፤”ድርብ፡ሠረዝ፡የ፡እነርሱን፡“;”semi-colon፥የእኛ“።”አራት፡ነጥብ፡ የእነርሱን፡“.”Full
stop ከተካ፡ከላይ፡ለተጠቀሰው፡የጽሑፍና፡የንባብ፡ማሳረፊያ፥ወይም፡ መግቻ፡የተጠቀምንበትን፡
የእኛን“፡”ሁለት፡ነጥብ፡የሚተካ፡ሌላ፡ነጥብ፡እነርሱ፡የላቸውም፡ማለት፡ነው።ከዚ.ህ፡ጋር፡ተያይዞ፡
እዚ.ህ፡ላይ፡ሊ.ወሳ፡የሚገባው፡ተመሳሳይ፡ቁም፡ነገር፡አለ፤ይኸም፡ለምሳሌ፡እኔ፡“እንደሆነ”፡ብዬ፡
አያይዤና፡አንድ፡አድርጌ፡የምጽፈውን፡ቃል፡“እንደ-ሆነ”፡ በሚል፡መልክ፡ለያይቶ፡የሚያቀርበው፡
የአጻጻፉ ችን፡ባህል፡ነው።ታዲያ!፡“እንደ-እዚ.ህ፡ከ-ሆነ፡ ለ-ምን፡ይኸው፡አጻጻፉ ችን፡እስከ-ዛሬ፡በ-
እነዚ.ህ፡እና፡እነዚ.ህን፡በ-መሰሉት፡ቃላት፡ላይ፡ሳይጸና፡ ቆየ?።በ-ቃላቱ፡ላይ፡የ-ሚቀጸሉት፥ወይም፡
የ-ሚ.ታዘሉት፡የ-አገባብ፡ዘሮች፡ከ-እነዚ.ህ፡ቃላት፡ ተለይተው፡እንዲ.-ጻፉ፡ስለ-ምን፡የ-ተገባ፡ሆነ?።
ሥርዓቱ፡ስለ-ምን፡በ-እዚ.ህ፡ዓይነት፡ሊ.ዘበራረቅ፡ቻለ?።ስለ-እዚ.ህ፡ይህም፡ችግር፡መፍትሔ፡
ሊ.ፈለግለት፡ይገባል።”፡በእኔ፡በኩል፡ለዚ.ህ፡ዝብርቅርቅ፡አጻጻፍ፡ያገኘሁት፡ማስተካከያ፡ከላይ፡
ተለያይቶና፡ተዛንቆ፡የተጻፈውን፡ዐረፍተ፡ ነገር፡ከዚ.ህ፡እንደ-ሚከተለው፡እንዲ.ህ፡በአንድ፡መልክ፡
አያይዞ፡እንዲ.ጻፍ፡ማድረጉ፡ነው፦“እንደዚ.ህ፡ከሆነ፡ለምን፡ይኸው፡አጻጻፉ ችን፡በእነ፡“እንደ፥ከ፥ለ፥
እስከ፥በ፥የ፥እንዲ.”፡እና፡“ስለ”፡በተባሉት፡በእነዚ.ህና፡እነዚ.ህን፡በመሰሉት፡ቃላት፡ላይ፡አልጸናም?።
በቃላቱ፡ላይ፡የሚ.ቀጸሉት፥ወይም፡የሚ.ታዘሉት፡የአገባብ፡ዘሮች፡፡ከእነዚ.ህ፡ቃላት፡ተለይተው፡
እንዲ.ጻፉ፡ስለምን፡ የተገባ፡ሆነ?።ሥርዓቱ፡ስለምን፡በእዚ.ህ፡ዓይነት፡ሊ.ዘበራረቅ፡ቻለ?።ስለዚ.ህ፡
ይህም፡ችግር፡ መፍትሔ፡ሊ.ፈለግለት፡ይገባል።”

ከዚ.ህ፡በላይ፡የ፡እርስዎን፡የ፡ገለበጠሰት፡ምክንያት፡እርሱ፡የ፡ነሰረንን፡ጥንታዊ፡አጻጻፍ፡
”ያልተሠሰረ፡ጥጎና፡አያስፈልገውም”፡ነው።እና፤ለዚ.ህ፡ዘመን፡ግራ፡የ፡ተጋሳ፡ትውልድ፡መንገድ፡
ማለት፡መሰላሻ፡ቀዳዳ፡መክፈት፡ነው።ብሎ፡ስለ፡እሚ.ገምት፡ስልቸዎን፡ለ፡መጠቀም፡አደገኛ፡መስሎ፡
ስለ፡ታዬው፡ስሜቱን፡ለ፡ማስታወቅ፡ነው።እንደ፡እርሱ፡አስተሣሠብ፡በነሰረሰት፡መ፡ቀጠሉን፡
ይመርጣል።እርስዎ፡በ-ዚ.ህ፡የተጠቀሙበትን፡በ፡ዚ.ህ፡ሲ.ጠቀም፡ከርሞ፡ነሰረ፡እና፡ደግ፡ነው።

የ፡ክቡር፡ሓዲስ፡ዓለማዬሁን፡ፊደሎቻችንን፡በተመለከተ፡ስሕተት፡ልኂደግመው፡የ፡እሚገሳን፡ አይመስለውም፡፡የ፡እርስዎንም፡ሆነ፡የ፡ሓዲስ፡ዓለማዬሁን፡ጥልቅ፡አስተሣሠብ፡የ፡እሚረ ዳ፡አሽ፡ ብሎ፡ለመገመት፡ይቸገራል፡፡

"ተመልክቼ፡አስተያየቴን፡እንድሰጥህ፡በእንግልጣሩ፡አነባበብ፡"ጽፌ፡ልኬልዎት፡ነበር!" ያልከኝ፡የኢትዮጵያኛ፡ፊደሎቻችን፡ሳይደርሱኝ፡ቀርተው፡ይሁን፥ወይም፡በሌላ፡ምክንያት፡ በመቀመሪያዬ፡ውስጥ፡ስላላገኘሁት፡ቅጂውን፡ልከህልኝ፡፡ለጥያቄህ፡አስፈላጊውን፡መልስ፡ብሰጥህ፡ ደስ፡ይለኛል"፡፡ስለ፡አሉት፡ደግሞ፡የነሰረውን፡ተንቀሳቃሽ፡መቀመሪያ፡ከ፡ቤተ፡መጻሕፍት፡ ስለ፡ተሠረቀ፡እና፡አሁን፡የ፡እሚጠቀምበት፡የ፡መስኮት፡፯፡መርሐ፡ግብሩን፡ሊቀበልሽት፡ስላልቻ ለ፡ ዘዴ፡ፈልጎ፡እና፡አስተካክሎ፡ሊልክልዎት፡ይጥራል፡፡እሹም፡ለ፡ፊደሎቻችን፡አነባበብ፡ነሰረ፡፡ ለምሣሌ፥ሰ>se ሱ>su ሲ>si ሳ>sa ሴ>sie ሰ>see ሶ>so አ>a ኡ>u ኢ>i ኣ>Aa ኤ>aie እ>Ee ኦ>o……በ፡መሳሽለ፡ሁኔታ፡ስለሺነህ፡ለማለት፥Seeleshineh

"እግዚአብሔር፡ለ፡ኢትዮጵያ፡የ፡መደበው፡"ቀኑ"፡እስኪ፡ደርስ፡ትዕግሥቱንና፡ጽናቱን፡ እንደ፡እሚያድልህ፡በማመን፡እጸልያለሁ፡፡በዚህ፡ረገድ፡በግልም፡ሆነ፥በማኅበር፡ጸሎታችን፡ ላይ፡ የ፡እምናደርገውን፡የ፡ተዘክሮ፡ስም፡አጠራርህን፡ለማስተካከል፡ይረዳን፡ዘንድ፡የቃል፡ኪዳን፡ ምስክርነቱን፡ሥርዓት፡ፈጽመህ፡የሰንደቅ፡ዓላማችንን፡(አረንጓዴ፥ብጫና፡ቀይ፡ቀለማት፡) ማተብ፡ በአንገትህ፡ያሠርህ፡መሆንህን፡ብታሳውቀኝ፡ደስ፡ይለኛል"፡፡ስለ፡አሉትም፣ልሳዊ፡ምስጋናውን፡ ያቀርባል፡፡

ሆኖም፣ስሜቱን፡በ፡አግባቡ፡ስለ፡ቀሰቀሱት፡አረንጓዴ፣ብጫ፡እና፡ቀይ፡ቀለማት፡ዓላማች ንን፡በተመለከት፡እንደ፡እሚከተለው፡ይገልጽልዎታል፥ማተብ፡ስለ፡መደረጉ፡ከ፡እርስዎ፡በ፡መማሩ፡ በ፡ይሳቤ፡ፍሥሐ፡ተቀብሎታል፡፡ከዚያ፡በፊት፡ግን፡አገሩን፡ከ፡ለቀቀ፡በኋላ፡እና፡የ፡እግዚአንሔር፡ የሽሹ፡የ፡ጋርዮሽ፡አኀዛዝ፡አገሩን፡ወረረ፡ከ፡ተባለ፡ጀምሮ፡እርሱነቱን፡ተነጥቆ፡ያለ፡ሀገሩ፡ኩራት፡ እና፡መብት፡ብሎም፡ነፃነት፡እንዳልተሰማው፡ተረድቶ፡ስለ፡አዘነ፡አጋጣሚ፡ባገኘ፡ቁጥር፡የ፡ሀገር፡ ልብሱን፡እና፡የ፡ዓላማውን፡ቀለማት፡እዬ፡ለበሰ፡ይሄዳል፡፡ጃፓን፡በነሰረበት፡ወቅት፡በ፡መንገድ፡ ሕፃናት፡"ሽንጎ፡ሳን"፡የ፡መኪና፡መቸላለፊያ፡መብራት፡ማለት፡ሲሆን፡አረንጓዴ፣ብጫ፡እና፡ቀይ፡ ዓላማችንን፡ቀለማት፡ለብሶ፡ስላዪት፡ነሰረ፡፡ከዚያም፡እስተ፡አሁን፡በ፡አንገቱ፣በ፡እጆቹ፡እንደ፡ አምሳር፤በቀለማቱ፡ኮፍያ፡ሠርቶ፡ዘውድ፡ጠልፎበት፡ታላቁ፡ንጉሥ፡እና፡ኢትዮጵያዊነት፡የ፡እሚል፡ ጽሑፍ፡የ፡ተጠለፈባቸው፡ያደርጋል፡፡እንደ፡ገናም፡ቀሚስ፡በቀለማቱ፡ሰፍቶ፡ስብሰባ፡ሲኖራቸው፡እና፡ አስተናጋጆች፡ከ፡አገራችን፡ሲመጡ፡ይለብሳቸዋል፡፡በትክሻ፡የ፡እሚለበስ፡ጉርድ፡ካባም፡ በ፡ቀለማቱ፡ሠርቶ፡አስቀምጦ፡በዓል፡ሲሆን፡ሰወች፡እንዲ፡ለብሱ፡ያደርጋል፡፡በ፡አንገቱ፡ካደ ረገው፡ ቀለማት፡ማተቡ፡የ፡ተሰኩት፡ሥነ፡ሥቅለት፡ያሸባቸው፡አክሊለ፡ሦክ፡እና፡ቀለበቶች፡ናቸው፡፡እናም፥ ሞቶ፡ለ፡ተነሣ፡ይህ፡ዓይነቱ፡አድራጎት፡ሲያንስ፡ነው፡፡

ለ፡መሆኑ፡እናንተ፡የምትሸጡት፡ኢትዮጵያኛ፡መዝገበ፡ቃላት፡አላችሁ፡ወይ?፡፡ከ፡ሊሊ፡የ፡ ቀረበሽት፡ጥያቄ፡ነው፡፡እኛም፣እርስዎ፡ቢ፡መልሱት፡ለ፡ሁላችንም፡ትምህርት፡ይሆናል፡፡"በድጋሚ፡ ምስጋና፡አቀርባለሁ፡፡የማላውቀውን፡እየተረዳሁ፡ በመምጣቴ፡ ሌላም፡ ተጨማሪ ሊብራራልኝ፡ የምፈልገው፡ የመኖር፡ ትርጉም፡ የምታውቀውን፡ ያህል፡ ጀባ፡ በለኝ"፡፡ የ፡እሚል፡ነሰረ፡እና፡ የ፡ኅዋ፡ሰሌዳዎን፡ልኳል፡፡

መዝገበ፡ቃላት፡ከ፡አገራችን፡እንዲ፡ገዛሽት፡ጠይቆ፡ከ፡መጣሽት፡የ፡ተሰማውን፡እኂሆ!፡ እንደ፡እሚከቸለው፡ስሜቱን፡ያኻፍለወታል፡፡እርእሱም፡ሳባ፡እንግሊዝኛ-ትግርኛ-አማርኛ- መዝገበ፡ቃላት፡በ፡እሚል፡ተጽፎ፥የ፡ተዘጋጀው፡በ፡ራሄል፡ጥላሁን፡መሆኑን፡ያበሥራል፡፡ከዚያም፥ የ፡አነባበብ፡መሰሪያ፥

| ትግርኛ፣ | አማርኛ፣ |
|---|---|
| ሀ። | ኸ። |
| ሃ። | ሀ። |
| ሐ። | ወፈር፡ያለ፡ኸ። |
| ሓ። | ወፈር፡ያለ፡ሃ። |
| ዐ። | ወፈር፡ያለ፡ኧ። |
| ዓ። | ወፈር፡ያለ፡ኧ። |
| ኸ። ምሳሌ፡በርኸ። | በርሄ። |
| በርሀ። | በራ። (ነጥቦቹ፡የ፡ተጻፉት፡በስለሺ.ነህ፡ነው።) |

በ፡ተጨማሪ፡በ፡አማርኛ፡ውስጥ፡'ኀ','ሠ','ጸ'፡ፊደላት፡በ፡ትግርኛው፡ውስጥ፡የሉም።ተጽፎ፡ሲ፡ያይ፡በጣም፡አዘነ።የ፡ሦስቱ፡ፊደላት፡አለ፡መኖር፡ብቻ፡ዓይደለም፡ግራሞቱ፡የ፡እንግልጣሩን፡",":ያለ፡እፍረት፡መጻፏ፡እንጂ!!።

እንደ፡እሚጎነዘበው፤በዛሬው፡አዲስ፡አበባ፡መካነ፡አእምሮ፡የ፡እሚሸጠው፡ትምህርት፡ጥራቱ፡አጠያያቂ፡መሆኑን፡ነው።በ፡ቋንቋ፡ጥናት፡ሰበብ፡ሁሉም፡እንዳፈነነው፡ፊደላቱን፡በጣጥሷቸዋል።የ፡እግዚአብሔር፡መንግሥት፡በ፡ኢትዮጵያ፡ነበረ፣አለ፣ይኖራልም።የ፡ጠፋው፡የ፡ስሕተቱን፡ንስሓ፡ገብቶ፡በ፡ኅብረት፡ተደማምጦ፡ፈጻሚ፡ፍጡር፡ነው።ኢትዮጵያ፡በ፡እግዚአብሔር፡መንግሥት፡ባትጠሰቅ፡ኖሮ፤እንደ፡ዩጐዝላቪያ፡ሆናም፡ነበረ።የ፡ኢትዮጵያ፡ሕዝቦች፡ያለ፡መንግሥት፡፳፡ዓመታት፡ገደማ፡እራሳቸውን፡በ፡እራሳቸው፡እያስተዳደሩ፡እናያለን።በዚህ፡ምክንያት፡የ፡ቻልነውን፡ከ፡ማድረግ፡አለ፡መቆጠቡን፡ስለሺ.ነህ፡ይመርጣል።በ፡ጎዋ፡ሰሌዳዎ፡የ፡እሚያደርጉት፡አሰራታች፡እና፡ተስፋ፡ሰጭ፡ስለ፡ሆነ፡እርስዎን፡እግዚአብሔር፡ያስንብትልን።

ትቼው፡በመምጣቴ፡ልቤን፡ከእናቴ፡ቤት፣
ለምትነግሩኝ፡ሁሉ፡በደንብ፡ደጋግሙት።

---

## ለአቶ ስለሺነህ ኹለተኛ እ-ጦማር፡ የተሰጠ መልስ።

፩. የልደትዎን ቀንና ብሔረ ሙላድዎን፥ የሕፃንነት ጊዜዎን ሳይቀር፡ ለትምህርት በኼዱበት አገር እስከገጠመዎ ፈተና፥ እስከዛሬ እያደረጉትና አኹንም እያካኼዱት እስካለው፡ የኢትዮጵያዊነትዎ ሕይወትና ተግባር ድረስ፡ ያለውን ዜና መዋዕልዎን፡ ባጭሩም ቢኾን በማስፈር፥ አንዳንድ የማናውቃቸውንና ትምህርታውያን የኾኑ ቍም ነገሮችንም አክለው በመግለጽ፡ በግንቦት ፲፪ ቀን፥ ፳፻፪ ዓ. ም. ለጻፉልኝ እ-ጦማርዎ፡ እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

፪. ባለፈው የመልስ ጽሑፌ ውስጥ፡ የአንተታውን አጠራር የቀጠልሁት፡ ቀደም ብሎ በደረሰኝ እ-ጦማርዎ ውስጥ፡ያነበብኋቸውን መግለጫዎችዎን፡ በትክክል ሳልገነዘብ፡ በመከተሌ ነበር፤ እነዚህም፡-

በመጀመሪያ፡ "...ለጃንሆይ፡አኀዛዝ፡ለኃ፡ወጣት፡ስለ፡ነሰርኩ፣ [ያ አገዛዝ] በቀላሉ፡እንደዚያ፡ተደርምሶ፤እንደዚህ፡አስከፊ፡ሁኔታ፡ይመጣል፡የእሚል፡ግምት፡አልነበረኝም።

”ቀጥሎ፡“...ምን፡ግዜም፡እግዚአብሔር፡ከክፉ፡ስለ፡እሚሰውረኝ፤ዐሥራ፡ ሁለተኛን፡በተፈሪ፡መኰንን፡የማታ፡ትምህርት፡ቤት፡ፈጽሜ፡በ፲፱፻፷፬፡ዓመተ፡ምሕረት፡ወጣሁ። በ፲፱፻፷፮፡አደገኛው፡ለውጥ፡ተደረገ።”

ከዚያም፡ “እስተ፡አሁን፡ባህላችንን፡እንደ፡እሚወዱት፡በማሰብ፡ዝም፡አልኩዎት፡ እንጂ፤አንተ፡እንዲሉኝ፡ልጽፍልዎ፡ካሰብኩ፡ቆይቻለሁ።እና፤ከአሁን፡በኋላ፡አንተ፡እንዲሉኝ፡ አደራዩ፡የጠበቀ፡ነው።” የሚሉት ቃልዎ ናቸው።

እነዚህን ዐረፍተ ነገሮች መሠረት በማድረግ፡ በእኔ በኩል ያሰላሁት የዕድሜ አገማመት፡ የተሳሳተ ኖርዋል። በዚሁ፡ በእኔ የተሳሳተ ግምት፡ የዕድሜዎን መጠን፡ ወስኜው የነበረው፡ ቢበዛ፡ በ፷ዎቹ ዓመታት ክልል ውስጥ እንደሚኾን ነበር።

በመጨረሻ ግን፡“ዕድሜ፡ካነሹ፡ዘንድ፤ስለሺነህ፡የ፡ተወለደው፡በ፡ሰኔ፡፳፡ለ፡፳፩፤እሑድ፡ ለ፡ሰኞ፡ጥባት፡፲፱፻፴፮፡ዓመተ፡ምሕረት፡ነው።” ብለው የጻፉልኝን ሳነብበው፡ የግምት ስሕተቴ፡ እርግጥ መኾኑን ተገነዘብሁ።

ለካ፡ በስሕተት፡ “አንተ!” እያልሁ፡ መጥራት የጀመርሁት፡ የአኹኑን የ፷፮ቱን የዕድሜ ባለጸጋ አዛውንት ኖርዋል። ባለማወቅ ላደረግሁት ስሕተት፡ እርስዎን ይቅርታ እየጠየቅሁ፡ እኔም፡ እንደእርስዎ፡ ለመልካሙ እግዚአብሔራዊው ባህላችን ቅድሚያንና ከበሬታን የምሰጥ ነኝና፡ ወደቀደመው አንቱታዬ መመለሴን ልገልጽልዎ እወድዳለሁ።

ይህንም ያደረግሁት፡ በደብዳቤዎ ውስጥ የሠፈረውን፡ እንዲህ የሚለውን፡ የራስዎን አስተሳሰብ፡እንደመመሪያ በመከተሌ ነው፡- “ስለሺነህ፡...አስተላልፎት፡የነሰረው፡ መልእክት፡ዕድሜውን፡በ፡መገሠት፡መነሻ፡አልነሰረም።የ፡ዋና፡ዓላማው፡ትኩረት፤እርስዎ፡ሥልጣኑ፡ እና፡በ፡ተግባርም፡ለ፡ኢትዮጵያችን፡እና፡ሕዝቦቿ፡የፈጸሟቸውንም፡ሆኑ፡እዬ፡ፈጸሙ፡ስለ፡ እሚገኙት፤የ፡እርስዎ፡እርስዎታ፡ስለ፡ከሰደው፡ነሰረ።”

እንግዴህ፡ ይህ አስተሳሰብዎ፡ ሊጸና የሚገባው፡ ለእኔ ብቻ ሳይኾን፡ (የእኔ ተግባር፡ በዚህ መልኩ፡ እኔን፡ ለእርስዎ እርስዎነት ካበቃ፡) በእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት እየፈጸሙት ያለውና የእኔኑ የመሰለው፥ ምናልባትም፡ ከእኔ ሊበልጥ የሚቻለው፡ የእርስዎ ኢትዮጵያዊ ተግባር ደግሞ፡ እርስዎንም፡ ለእኔ እርስዎታ የማያበቃበት፡ ምንም ምክንያት የለም፤ ስለዚህ ነው፡ ወደቀደመው እርስዎታዬ ተመልሼ፡ እርስዎን፡ “እርስዎ!” እንድል አግባብ ኾኖ ያገኘሁት፤ እና፡ እኔ፡ የእርስዎን ውሳኔ ተቀብዬ፡ “አንተ!” ማለቱን ጀምሬው እንደነበረ፡ እርስዎም አኹን፡ይህን ውሳኔዬን፡ ያለቅርታ ይቀበሉኝ ዘንድ እጠይቅዎታለሁ።

፫. በፈረንጆቹ ቋንቋ፡ የፊደሎቻችንን አነባበብ በሚመለከት፡ “ለምሣሌ፥ሰ>se ሱ>su ሲ>si ሳ>sa ሴ>sie ስ>see ሶ>so አ>a ኡ>u ኢ>i ኣ>Aa ኤ>aie እ>Ee ኦ>o……በ፡መሳሸለ፡ሁኔታ፡ስለሺነህ፡ለማለት፥Seeleshineh” ብለው ያቀረቡት አሳብ፡ ለኢትዮጵያኛው ፊደል መክተብያና መቀመርያ ተብሎ፡ በዘመናዊው ኪነ ጥበብ፡ የተበጀው መሣርያ የሚጠቀምበትን ስልት የተከተለ መልካም ማማረጫ ነው።

እዚህ ላይ፡ በእኔ በኩል የማክለው፡ እንዲህ የሚል፡ አስተያየት አለ፡- እነርሱ (ፈረንጆቹ)፡ ለሰባቱ ኹሉ የአሌፋታችን ሆህያት፡ የሚበቃና የሚስማማ ሆሄ ስለሌላቸው ነው እንጂ፡ ለምሳሌ፡“ኧ” የሚለውን የመሰለ ግዑዝ ድምፅ ካለውና እንደዚያ ከሚነበብ፡ ከግእዙ፡ ማለትም፡ ከመጀመሪያው ሆሄ ጋር፡ የሚነጻጸር፡

የራሳቸው ሆሄ ቢኖራቸው ኖሮ፥ እነዚህኑ አሌፋታቸውን፡ እንደእኛዎቹ የመጀመሪያዎቹ ግእዝ ሆህያት፡ ቋሚና መነሻ አድርገው፡ A=ኧ U=ኡ I=ኢ Aa=ኣ E=ኤ ‘=እ O=ኦ ብለው በመመደብ፥ በሌሎቹ ግዑዛን አሌፋታቸውም ላይ፡ እንደእኛ ነቍጦችና ሠረዞች፡ በመለጠፍ፡ አናባቢ ኾነው ሊያገለግሏቸው በቻሉ ነበር።

ይህም ማለት፡ የእነርሱ A ወይም a እና B ወይም b፡ እንደእኛ “ኧ” እና “በ” ተብለው፡ ለአሌፋቱ፡ መደበኛ መነሻ ኾነው፡ በግዑዙ፥ ወይም፡ በግእዙ ድምፅ፡ የሚነበቡ ቢኾን ኖሮ፡ ፊደሎቻቸው ኹሉ፡ እንደኢትዮጵያኛው አሌፋት፡ ለምሳሌ፡ B=በ Bu=ቡ Bi=ቢ Ba=ባ Be=ቤ B’=ብ Bo=ቦ ተብለው ሊነበቡና ሊጻፉ፡ ቀና በኾነ ነበር ማለት ነው።

ነገር ግን፡ ከመሠረቱ፡ ይህን የእኛን የመሰለውን ሥርዓት ስላልተከተሉ፡ በዚህ ዘዴ የመጠቀሙ ምርጫ፡ ለእነርሱ ሊሠራላቸው አልተቻለም። ስለዚህ፡ አኹን ያለው ምርጫ፡ የእርስዎን የመሰለውን ስልት መከተሉ ብቻ ነው።

፬. ”ያልተሠሰረ፡ጥጎና፡አያስፈልገውም”፡ ያሉትን ይትበሃል፡ “ያልተሠበረ፡ ጥንቃቄ፥ ጥበቃና ማጠናከርያ እንጂ፡ ጥገና አያስፈልገውም!” በሚሉ ቃላት ላሚላውና ላብራራው እወድዳለሁ። በኢትዮጵያዊው ፊደላችንና ሥነ ጽሑፋችን ቅርስ ላይ፡ እርስዎም፥ እኔም፡ በአስተዋጽዖዋችን እያካኼድን ያለነው፡ ይህንኑ ነውና።

፭. እኛ፡ በአኹኑ ጊዜ የምንሸጠው ኢትዮጵያኛ መዝገበ ቃላት የለንም። ወደፊት አዘጋጅተን ለማሳተም ግን፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንጠብቃለን።